# በ.ኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ የሥራ ስምሪትና የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ የተሰጠ ግብረ-መልስ

1. **መግቢያ**
2. በ.ኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 17 ከተሰጡ ተልዕኮዎች ውስጥ አንዱ አስፈፃሚ አካላትን መከታተልና መቆጣጠር ሲሆን በም/ቤቱ አሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 እና በተሻሻለው አንቀፅ 172 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከሚከታተላቸው ተቋማት አንዱ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ነው፡፡ ከቋሚ ኮሚቴው የክትትል አግባቦች መካከል የተቋማትን ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት ተቀብሎ በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት ሲሆን በዚህም መሠረት የተቋሙን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በመመልከት ዋና ዋና ጥንካሬዎችን፣ እጥረቶችንና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት ግብረ-መልስ ሰጥቷል፡፡

3. <u>ዕቅድን ለመገምገም ታሳቢ የተደረጉ</u>
   - ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት ከተቀመጡ ግቦችና አቅጣጫዎች፣
   - የተቋሙን የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ ዝግጅት መነሻ አድርጓል።
4. <u>በዕቅድ ዝግጅት የታዩ ጥንካሬዎችና በእጥረት የተለዩ ጉዳዮች</u>

   4.1 . <u>በጥንካሬ የተለዩ ጉዳዮች</u>
   - ተቋሙ አዲስ እንደ መሆኑ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ የተደራጀ ግቦችንና አቅጣጫዎችን የዕቅዱ አካል ማድረጉ፣
   - ተቋሙ ዋና ዋና ግቦችንና ተልዕኮዎችን መነሻ በማድረግ ዓመታዊ ዕቅዱ መዘጋጀቱ፣

     <u>ለአብነት፡-</u>
     - በተዘጋጀው ዕቅድ በዘርፉ ስትራቴጅና ማዕቀፍ ላይ ለ23,000 አመራሮችና ባለሙያዎች ለ3,702,720 ሥራ ፈላጊዎች የግንዛቤ

ማስጨበጫ ስልጠና በኢንተርፕራይዝ የሂሣብ አያያዝና ምርመራ አገልግሎት ላይ እንደሚሠጥ መያዙ፣

- የተለያዩ ስልጠናዎችን ለመስጠትና አቅም ለመገንባት በዕቅድ መያዙ ፣
- የአሠሪና ሠራተኞች በነፃነት ተደራጅተው መብታቸውን እንዲጠቀሙ እና በህብረት እየተደራደሩ ጥቅማቸውን እንዲያስከብሩ የምክክርና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ለማዘጋጀት መታቀዱ፣

❖ የአሠራር ሥርዓት የሚያሻሽሉ ፖሊሲ ደንብና መመሪያዎችን በማዘጋጀት በማፀደቅ ወደ ስራ ለመግባት በዕቅድ መያዙ፣

## 4.2 . <u>በዕጥረት የተለዩ ጉዳዮች</u>

❖ ተቋሙ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ባለመኖሩ የ2014 ዓመታዊ ዕቅዱ ከ10 ዓመቱ የልማት መሪ ዕቅድ የተቀዳ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣

❖ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድን ለፌደራልም፣ ለክልሎች እና ለአጋር አካላት ተደራሽና አሣታፊ ለማድረግ የሚከተሉት አቅም የመገንባት አቅጣጫ በዕቅዱ ላይ አለመመላከቱ፣

❖ ከአጋር አካላት ጋር በተናበበና በተቀናጀ መልኩ የታቀደ ስለመሆኑ አለመመላከቱ፣ በተለይም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ጋር ትስስሩ በግልፅ አለመመላከቱ፣

❖ የ2014 ዓመታዊ ዕቅድ ከ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም ያደገ መሆን ሲገባው የተዘጋጀው ዕቅድ ያነሠ ሆኖ መታቀዱ፣

<u>ለአብነት</u>፡-

❖ በ2014 በጀት ዓመት ለ3.1 ሚሊዬን ሥራ ፈላጊዎች ምቹ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የታቀደ ቢሆንም በ2013 ዓመታዊ አፈፃፀም ደግሞ 3,457,988 ለሆኑ ሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል መፈጠሩ የዚህ በጀት ዕቅድ አንሶ መታቀዱ፣

❖ የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸውን ኢንተርፕራይዞች እውነታውን ለማረጋገጥና ጥራቱን ለመለካት የተለየ ስልት አለመቀመጡ፣

- ❖ የቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች መረጃን መሠረት በማድረግ በየስራ ዘርፎች፣ በገጠርና በከተማ ተለይቶ በዕቅዱ ላይ የተመላከተ አለመሆኑ፣

❖ የተዘጋጀው ዕቅድ በቦታ፣ በመጠንና በስም ተለይቶ የታቀደ አለመሆኑ፣

<u>ለአብነት</u>፦

- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያና የአቅም ግንባታ ስልጠና፣ ለተቋም አስፈፃሚና ፈፃሚ ስልጠና መስጠት ወዘተ… በመቶኛ መቀመጡ (ገፅ 34)፣
- ለባለሙያዎች የተሠጠ የመረጃ አያያዝ ስልጠና መለኪያ ክልል ተብሎ በዕቅዱ 100 ተብሎ መያዙ (ገፅ 37)፣
- በጥቅሉ ለአመራሮችና ሙያተኞች እንዲሁም ለሥራ ፈላጊዎች የግንዛቤ ስልጠና ለመስጠት የታቀደ ቢሆንም በፌደራል፣ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተለይቶ አለመታቀዱ (ገፅ34)፣

❖ በበጀት ዓመቱ ከዚህ በፊት የተሠጠውን መደበኛና ተዘዋዋሪ ብድር 100% ለማስመለስ የታቀደ ቢሆንም የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም ደግሞ 27% ብቻ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን በቀጣይም ብድሩን 100% ለማስመለስ የሚጠቀሙትን ስልት አለመመላከቱ፣

❖ የተዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ ከሩብ ዓመቱ ዕቅድ ጋር የማይናበብ መሆኑ

**ለአብነት፣**

- የማስፈፀም አቅም ግንባታ ላይ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያና የአቅም ግንባታ የሚወስዱ አሠልጣኞች በመቶኛ የዓመቱ 15% ሆኖ በሩብ ዓመቱ 45% መታቀዱ (ገፅ 34)
- በኢንደስትሪ ትግበራ ልምምድ ያደረጉ አሠልጣኞች በበጀት ዓመቱ 10% ታቅዶ በሩብ ዓመቱ 40% ተብሎ መታቀዱ (ገፅ 34)፣

❖ ከፌደራል እስከ ታች ድረስ ተግባሮችን ውጤታማ የሆነ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በዕቅዱ ላይ አለመመላከቱ

**ለአብነት፦**

- ❖ በፌደራል ደረጃ ወደ ታዳጊ መካከለኛ ለተሸጋገሩ 150 ኢንተርፕራይዞችና የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ 72 የአንድ ማዕከል

አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችንና 72 ባለሙያዎችን ዕውቅናና ሽልማት እንዲሰጣቸው ለማድረግ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን በለየ መልኩ የታቀደ አለመሆኑ፣

- ❖ በየአካባቢው የግብርናና ማኑፋክቸሪንግ ምርቶች ተመርተው የገበያ ትስስር ስለማይፈጠርላቸው እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ ስለማይደረግ በድካማቸው ልክ አለመጠቀማቸውና ለዚህም የተሟለጠ የገበያ ትስስር ለማከናዎን አዲስ የአሠራር ስልት አለመቀመጡ፣
- ❖ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን ሥራ ፈላጊዎች መረጃ በተደራጀ መንገድ ሥለማይያዝ በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው እንዲሠሩ ለአምስት ዓመት ከተፈቀደላቸው በኋላ የሥራ አገልግሎት ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ሽግግር ሣይደረግላቸው በያዙት ቦታና ስራ ሲቀጥሉ ይታያሉ። ይህን ችግር የሚፈታ ስልት በዕቅዱ ላይ አለመመላከቱ፣
- ❖ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው በቂ ካፒታል ከፈጠሩ በኋላ አጠናክሮ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገሩ በተቋሙ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ ክፍተት መኖሩ፣
- ❖ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የክህሎት ስልጠና ስራ ዕድል ለሚፈጠርላቸው ዜጎች ስልጠናው በቂ ስለመሆኑ የመከታተያ ስልት አለመቀመጡ፣
- ❖ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ገበያው የሚፈልገውን የሰው ሀይል በማምረት እና የገበያ ትስስር ለመፍጠር የገበያ ጥናቶችን በመዳሰስ ጉድለቱን በሚሞላ አግባብ ለመፈፀም የሚያስችል ስልት አለመኖሩ፣
- ❖ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የስራ ዕድል ለሚፈጠርላቸው ዜጎች የክህሎት ስልጠና ሲሰጥ የመምህር ተማሪ ጥምርታን በዕቅዱ ላይ ያመላከተ አለመሆኑ፣

- ❖ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሽታን ለመከላከል የሚያስችል ዕቅድ በበጀት ዓመቱ አለመታቀዱ፣
- ❖ የሚታዩ ብልሹ አሠራሮችን በልዩ ትኩረት ከላይ እስከታች ለመቅረፍ የሚያስችል አመላካች የሆነ ዕቅድ አለመዘጋጀቱ፣

**ለአብነት**:.

- ሥራ ፈላጊዎች ሲደራጁ በአድሎዓዊነትና በመቀራረብ አደራጆች በማይገባ መልኩ ለመጠቃቀም የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ስልት ጨምሮ የዕቅድ አካል አለማድረግ

❖ ተግባሮቹ በዕቅድ ደረጃ የተመላከቱ ቢሆንም ዕቅዶችን ማስፈፀም የሚያስችል የበጀት ፍላጎት አለመካተቱ መሠረታዊ ክፍተት መኖሩ

4. **ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

❖ የ2014 በጀት ዕቅድን ለመገምገም ያስችል ዘንድ የተቋሙን የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደተግባር እንዲገባ ማስቻልና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መላክ ይገባዋል፡፡

❖ ከፌደራል እስከ ታች ድረስ ተግባሮችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በዕቅዱ ላይ ማካተትና የዕቅዱ አካል ማድረግ ይገባል፣

❖ ወቅቱ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሽታ እየተስፋፋ  በመሆኑ የተቋሙን ሰራተኞችንም ሆነ ሌሎች ተገልጋዮችን ወረርሽኙ ለመከላከል የሚደረጉ ተግባራትን የዕቅዱ አካል ሊደረግ ይገባል።

❖ ብልሹ የአሠራር ምንጮችን በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ሊፈቱ የሚገቡ ጉዳዮችን በዝርዝር በመለየትና በጥናት በተደገፈ መልኩ ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችል የአሠራር ስልት መከተል ይገባል።

❖ በዕቅዱ ያልተካተቱና ከዕቅድ ማነስ ጋር የተመላከቱ ጉዳዮችን ለይቶ ዕቅዱን በመከለስ  ማካተትና የዕቅዱ አካል እንዲሆን ማስቻል ይገባል፣

❖ በተቋሙ የታቀዱትን ዝርዝር ተግባራት በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ለማስፈፀም በጀት አስፈላጊ በመሆኑ በዕቅዱ ላይ እንዲመላከት ቢደረግ፣

❖ በሀገራችን ላይ  በተፈፀመው ወረራ ምክንያት የወደሙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከክልሎች ጋር በመተባበር በመጠገንና በማደራጀት ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችሉ ተግባራት የዕቅዱ አካል ቢደረጉ፣

**5. ማጠቃለያ**

ተቋሙ አዲስ በሚኒስቴር ደረጃ የተቋቋመ እንደመሆኑ መጠን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ለማዘጋጀት መሞከሩ ጥሩ ሆኖ ነገር ግን በዕቅዱ ያልተካተቱና ዝቅተኛ እንደሆኑ የተመላከቱትን ጉዳዮችን በማካተት ዕቅዱን እንደገና በመከለስ እንዲሁም በቀጣይ ጊዚያት በድርጊት መርሀ ግብሩ መሠረት ዕቅዱን ለማስፈፀም በትኩረት ተይዞ መሠራት ይገባዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የዜጎችን ስራ አጥነት ለመቅረፍ፣ የሚያስችልና የባህሪ ለውጥ የሚያመጣ ስልጠና በመስጠት ብልሹ አሠራሮችን የማስወገድ ተግባራት ልዩ ድጋፍና ክትትል እንደሚያስፈልግ ቋሚ ኮሚቴው አመላክቷል።